



የዛሬዋ እንግዳችን ቤተሰባቸውን በጨቅላ እድሜያቸው በሞት ያጡት እና በዚሁ ሳቢያ ወደ ፈረንሳይ ሀገር ለትምሕርት በወሰዷቸውና በኢትዮጵያ አየር መንገድ አማካኝነት የፈረንሳይ ቴሌቭዥን ቻናል ሁለት ባዘጋጀው ዓለም አቀፍ የቁንጅና ውድድር ላይ ተወዳድረው ከነበሩትና በሥልጣኔ ከገነኑት ከ35 ሀገራት ከመጡት ተወዳዳሪዎች መካከል ኢትዮጵያን ወክለው ተወዳድረው በአንደኛነት ያሸነፉት የዛን ጊዜዋ የ16 ዓምቷ ታዳጊ ወጣት ወ/ሮ የሐረርወርቅ ጋሻው ናቸው። በዚህም የመጀመሪያዋ ጥቁር የዘመኑ የአውሮፓ ቆንጆ ከመሆናቸውም በሻገር ለበርካታ ውድ ጌጣጌጦች የዘመኑ ውድ ሰዓቶች ወዘተ ሁሉ የመጀመሪያዋ ጥቁር ሞዴል በመሆን የሰሩ ናቸው። ወ/ሮ የሐረርወርቅ ጋሻው የቀድሞውን የኢትዮጵያ ፕ/ት ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያምን በመጠየቅ በኢዮጵያ በአውሮፕላን አደጋ ሕይወታቸውን ያጡት የአሜሪካ የምክር ቤት አባል ሚኪ ላንድ እና ለሞቱት ኢትዮጵያውያን በቅ/ ሥላሴ ቤ/ክ ፀሎተ ፍትሐት እንዲደረግላቸው በማድረግ በሁለቱ ሀገራት መካከል የነበረውን ዲፕሎማሲያዊ ውጥረት እንዲረግብ ያደረጉ ናቸው ።

ወ/ሮ የሐረርወርቅ ጋሻው ወያኔ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ለሁለት በከፈለበት ጌዜ በራሳቸው ወጪ አትላንታ ላይ የሆቴልና የአዳራሽ በመሸፈን አቡነ ጳውሎስንና አቡነ መርቆሪዎስን ከበርካታ ብፁዓን አባቶችን ጋር ሰብስበው እርቀሠላሙን የጀመሩ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በስደት ይኖሩ የነበሩ አቡነ ይሥሃቅና ሌሎችም የሃይማኖት አባቶች ደሞዝ እንዲከፈላቸው ያደረጉ ናቸው።ወ /ሮ የሐረር ወርቅ ጋሻው ገና በ20ዎቹ እድሜያቸው የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ሴቶች ለሰላምና ለዲሞክራሲ የሚል የፖለቲካ ድርጅት ያቋቋሙ፤ በአሜሪካ ሕግ መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግሥትን ያቋቋሙ፤ የኢትዮጵያንና የኤርትራን መንግሥታት እርቅ የጀመሩ፤ በተለያዩ ሃገራት በስደት ይሰቃዩ የነበሩ ኢትዮጵያውያንና አፍሪካውያን ወደ አደጉ አገራት እንዲመጡ ያደረጉ፤ በኤርትራ እና በኢዮጵያ ውስጥ ይገኙ የነበሩትን የጦር ምርኮኞች ያስለቀቁ፤ ከድሮ እስከ ዘንድሮ ፓንአፍሪካኒዝም አሁን የደረሰበት እንዲደርስ ትልቁንና ዋናውን ሚና የተጫወቱ፤ በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዘዳንድት ኔልሰን ማንዴላ የአፍሪካ የጥቁር አልማዝ ተብለው የተሞካሹ በሀገር ቤትም የኢትዮጵያ ወርቅ የሚባሉ ናቸው።

እነሆ በመደበኛውና በሳምንታዊው ረቡዕ September 16,2020 ልክ 5PM PST (8PMEST) ሰዓት ላይ እንወያይ ዘንድ በአክብሮት ተጋበዛችኋል። ስልክ ቁጥር 1 848-220-3300 የማለፊያ ቁጥር (ID) 570 9144 ለጥያቄ (አስተያየት) *5 ይጫኑ።

አዘጋጅ፡- ባልደራስ ላስ ቬጋስ